


# ቤታር

# ቤታር




## <u>የቤታር ታሪክ በአጭሩ - היסטוריה של ביתר בקצרה</u>

ቤታር ወይም በረጅም ሥሙ "የዕብራውያን ወጣቶች ቃል ኪዳን በዮሴፍ ትሮምፔልዶር ሥም የተሰየመ ነው. ስለ አቶ ዮሴፍ ትሮምፔልዶር ማንነት በሌላ ጽሑፍ ተመልከት.

ቤታር የጽዮናዊያን ወጣቶች ብሔርያዊ ድርጅት ሲሆን፡ በአሁኑ ጊዜ ድርጅቱ በእስራኤል ሀገር እና በውጭ ሀገሮች ላይ በሚገኙት ይሁዳዊያን ሕብረተሰቦች የጽዮናዊ እንቅስቃሴና ትምህርት የሚሰጥ ወኪል አለው፡ ቤታር የተቋቋመው በሕዳር ወር በ1923 ዓ.ም በሪጋ ከተማ በላትቪያ ሀገር ሲሆን. ድርጅቱን ያቋቋመው አቶ ዜኤብ ዤቡቲንስኪ ሲሆኑ. እሳቸውም እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ የቤታር ታልቁ መሪና ባላባራስ ነበሩ.

ድርጅቱ የተቋቋመበት ምክኒያት ስለ ጽዮናዊያን እንቅስቃሴ ሲሆን. ዋናው አልማ ወታደራዊ በርጌድ ለማሰልጠን፡ ከዛም በኋላ በእስራኤል ሀገር ከነበሩት የይሁዲዎች የመከላከያ በርጌዶች ጋር አብሮ በመሰታፍ፡ በዓለም ተበታትኖ ለሚገኘው ለእስራኤል ሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታ እንድትሆን እስራኤል ሀገር ለማቋቋም ነው. ይሄን ለማድረግ በዚያን ጊዜ ሀገሯ በዓረቦችና በእንግሊዞች ቁጥጥር ስር ስለነብረች.ሀገሯ በይሁዲ እጅ ለማድረግ ከዓረቦችና ከእንግሊዞች ጋር ብዙ ጦርነትና ግጭት አሳልፈዋል.

በላትቪያ ሀገር ድርጅቱ በድንብ ከተቋቋመ በኋላ በ1926 ዓ.ም የመጀምርያ ቡድን ወደ እስራኤል ሀገር በመምጣት በፔታሕ ቲክባ "የመብራት ቡድን" የተባለ ፈጣኝ የምስረታ ሥራዎችን ጀመረ. እስከ 1928 ዓ.ም ከፖላንድ ከሮማንያ ከችኮስሎቫኪያ ከሁንጋሪያ ከሊታ ከጀርመን ከፈረንሳይ ከእስራኤል ከነዚህ ሀግሮች የተወጣጡ ጽዮናዊያን ወጣቶች ወደቤታር ተጨምረዋል.

እስራኤል ሀገር ከተቋቋመች ከአንድ ዓመት በኋላ ስለ ድርጅቱ ሁኔታ ታላቅ ዓለም አቀፍ ስብሰባ ተደረገ. ብዙኃን ሰወች ድርጅቱ ይፈርሳል በማለት ቅሬታ ተሰምቷቸው ነብር
ምክኒያቱም የድርጅቱ ሁለት አበትይ ዓላማዎች ተሳክተዋል፡
1ኛ፡ ሀገሯን ለማቋቋም የተደረገው ትግል ተሳክቶ. እስራኤል ተመስርታለች
2ኛ፡ ወታደራዊ ድርጅት አልፎ- ትልቅ የጦር መከላከልያ ኃይል "ጽባ ሀጋና ለእስራኤል" ተቋቁሟል
በመጨረሻ ግን የቤታር ድርጅት አቅጣጫው ተቀይሮ በሌላ ጉዳዮች አተኮረ፡
በአለፉት ዓመታት የይሁዲን የሰፈራ ጣኒያ ግንባታ ምስረታ በሀገሯ ማጠንከር ሲሆን፡
የጽዮናዊያንን ትምህርት በእስራኤል እና በዓለም ይሁዳዊያን ላይ ማሰራጨት ነው.
ዛሬ ግን ቤታር እንደሌሎች የወጣቶች ድርጅቶች በመሆን በማንኛውም ጉዳይ በእስራኤል በተለያዩ ከተሞች እና በውጭ ሀገር በይሁዲዊያን ሕብረተሰቦች የተለያዩ ተግባሮችን እንቅስቃሴ ያደርጋል.
ስለ ቤታር ሰፊ መረጃ ለመቀበል በዚህ http://www.betar.org.il/ ኢንተርነት አድራሻ ይመልከቱ.

ከአክብሮት ጋር

አበጀ መድኃኔ የቤታር አላፊ ወይም ተወካይ በረሆቦት ከተማ
אבג'ה מדהני רכז מעו"ז ביתר ומגשר קהילתי ברחובות
פל'/ስል 050-6348865/ מייל: aveje@betar.org.il